9- ክፍል 3 አንቀፅ 18 ስር ያሉ ንኡስ አንቀፆች ተሰርዘዉ በሚከተሉት ንዑስ አንቀጾች ተተክቷል::

1- የቦርዱ ተጠሪነት ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይሆናል::

2- የቦርዱ አባላት የስራ ዘመን የክልሉ መንግስት በሚያወጣዉ ደንብ ይወሰናል::

3- የቦርዱ አባላት የሚከተሉት ይሆናሉ::

ሀ- የክልሉ ምክር ቤት ሊቀመንበር ................................ሰብሳቢ

ለ- የኢኮኖሚ ዘርፍ ኃላፊ ....... አባል

ሐ- የዉ/ል/ማ/አ/ቢሮ ኃላፊ ... አባል

መ- የሥ/ከ/ል/ቢሮ ኃላፊ ....... አባል

ሠ- የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት ሹም ................................ አባል

ረ- እንደ አስፈላጊነቱ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰይመዉ አንድ አባል ................................ አባል

ሰ- የባለስልጣኑ ስራ አስኪያጅ ... ፀሀፊ እና አባል

10- ክፍል 3 አንቀፅ 20 ንዑስ አንቀፅ 1 በሚከተለዉ መልኩ ተሻሽሏል::

«የባለስልጣኑን የስራ እቅድ መርምሮ ይወስናል: እንደ አስፈላጊነቱ ከክልሉ መንግስት ድጎማ በጀት ሲጠይቅ ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አቅርቦ ያጸድቃል:: »

11- ክፍል 3 አንቀፅ 24 ንዑስ አንቀፅ 1.2.3.4 ተሰርዘዋል::

12- ክፍል 5 አንቀፅ 30 ንዑስ አንቀፅ 2 ተሰርዘዋል::

13- ክፍል 5 አንቀፅ 33 በሚከተለዉ መልኩ ተሻሽሏል::

«አዋጅ ቁጥር 2/1988 አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ 6 በዚህ አዋጅ ተሽሯል::

ሐረር ግንቦት 9 ቀን 1992 ዓ.ም

ጋዛሊ መሐመድ

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ፕሬዝዳንት